# “ቤተ-ክርስትያን”

ለዘመናት፡ጥላ፡ሆና፤
ስትራዳ፡ከፈተና፤
በዕውቀት፡አጎልምሳ፤
በጥበብ፤አጎናፅፋ፤
እየሰጠች፡ፀጋ፡ተስፋ፤
ድካም፡አታውቅ፡አይታክታት፡
ፊቷ፡በርቶ፡በፈገግታ፤
ስትጠብቅ፡ቤቷን፡ከፍታ፤
ስንቱ፡አለፈ፤
ስንቱስ፡አረፈ፤
የልቡን፡አሚልታለት፤
ስትድረው፡ስትኩለው፤
ሰው፡አድርጋ፡ስትሸኘው፤
ማንነቱን፡ስታሳየው፤
አቤት፡ላያት፡ላስተዋላት፤
ስንዱ፡እኮ፡እመቤት፡ናት።
የጉዞዬ፡ምልክቴ፤
የእምባዬ፡አባሽ፡መድኈኒቴ፤
የሩጫ፡ፍፃሜዬ፤
ንፁህ፡መስዋዕት፡የዓላማዬ፤
ብቸኛ፡ሰሚ፡የእንጉርጉሮዬ፤
እያለ፡ሲያወያያት፤
በነፍስ፡ወከፍ፡የኔ፡ሲላት፤
እያጣፈጠ፡ስሟን ሲጠራት፤
በዕልልታ፡ሲቀባበላት፤
በዝማሬ፡ሲያስተጋባት፤
በአማረ፡ቃል፡ሲሰማማት፤
ጆሮ፡ዳባ፡መች፡ታውቅና፤
ትደርሳለች፡ቀድማ፡ፈጥና፤
አቤት፡ብላ፡ልታፅናና፤
የመልካም፡ሰው፡መልካም፡ስፍራ፤
የደጋጎች፡በር፡መግቢያ፤
ከጥቂቱ፡ብዙ፡አፍርታ፤
ለብዙዎች፡ሆና፡አለኝታ፤
ኮትኩታ፡አዘጋጅታ፤
በንስሃ፡ሁሉን፡ጠርታ፤
ለሰማያዊው፡ክብር፡አጬታ፤
ይኸው፡ታየ፡የሷ፡ውለታ፤
የቤተክርስትያን፡እናትነቷ።
ደረቷ፡ስር፡ተለጥፈን፤
ስንመገምግ፡በህብረት፡ሆነን፤
ጡቶቿ፡መች፡ደረቁ፤
ወተት፡ከመስጠትስ፡መቼ፡ራቁ፤
ብሉይን፡ከሐዲሱ፤
እያስማማች፡ስታስተምር፤
የምስራች፡ስትነግር፤
ስትገስፅ፡ስትመክር፤

የተጣላን፡ስታስታርቅ፤
በጎውንም፡ስትመርቅ፤
ምግባር፡ከሐይማኖት፡ስትጠነቅቅ፤
ምስጢራትን፡ስታራቅቅ፤
ይኸው፡ነው፡አለች፡የኔ፡ድርሻ፤
ከልጅነት፡ እስከ፡እውቀት፤
ለእኛ፡እንዲሆነን፡መዳረሻ።

ከኃይለመስቀል፡ተስፋዬ
ለንደን